# ለክልል ወሳኝ ኩነት መዝጋቢ ተቋማት የተዘጋጀ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ አፈጻጸም መመሪያ

**ቁጥር 7/2010 ዓ/ም**

**ለክልል ወሳኝ ኩነት መዝጋቢ ተቋማት የተዘጋጀ የወሳኝ ኩነት**

**ምዝገባ አፈጻጸም መመሪያ**

**ቁጥር 7/2010**

የፌደራል ወሳኝ ኩነት ምዝገባ ኤጀንሲ በወሳኝ ኩነት ምዝገባና የብሄራዊ መታወቂያ አዋጅ ቁጥር 760/2004 አንቀጽ 70(2) በተሰጠዉ ስልጣን መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

**ክፍል አንድ**

**ጠቅላላ ድንጋጌዎች**

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "**የወሳኝ ኩነት ምዝገባ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር** 7/2010" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ትርጓሜ

በሌሎች ህጎች የተሰጠው ትርጓሜ እንደተጠበቅ ሆኖ የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጓሜ የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. **"ልደት"** ማለት የእርግዝና ጊዜው ግምት ውስጥ ሳይገባ ህፃኑ ከእናቱ ማህፀን እንደወጣ ወዲያውኑ ሕይወት ያለው መሆኑ ሲታወቅ ነው።
2. **"ሞት"** ማለት አንድ በሕይወት ይኖር የነበረ ሰው በሕይወት ያለ መሆኑን የሚያሳውቁ ምልክቶችን ሙሉ በሙሉ ለዘለቄታው ሲያጣ ነው።
3. **"ጋብቻ"** ማለት ዕድሜአቸው 18 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆኑ አንድ ወንድና አንዲት ሴት አግባብ ባለው ህግ መሰረት ባልና ሚስት መሆናቸው ሲረጋገጥ ነው።
4. **"ፍቺ"** ማለት አግባብ ባለው ህግ መሰረት ተፈፅሞ የነበረ ጋብቻ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት የፍቺ ውሳኔ ሲሰጥ ነው።
5. **"ጉዲፈቻ"** ማለት አግባብ ባለው ህግ መሰረት የራስ ያልሆነን ልጅ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት በፀደቀ ስምምነት የራስ ልጅ ማድረግ ነው።
6. **"ልጅነትን መቀበል"** ማለት አንድ ሰው አንድን የተወለደ ልጅ የእርሱ ልጅ መሆኑን አግባብ ባለው ህግ መሰረት አምኖ ቃሉን ሲሰጥ ነው።
7. **"አባትነትን በፍርድ ቤት ማወቅ"** ማለት የልጅ አባት ያልታወቀ ወይም የተካደ ከሆነ የልጁ አባት ማን እንደሆነ በፍርድ ቤት ውሳኔ ሲረጋገጥ ነው።

8. **“ጋብቻ ሳይፈፀም እንደ ባልና ሚስት መኖር”** ማለት አንድ ወንድና አንዲት ሴት በሕግ በሚፀና አኳኋን ጋብቻ ሳይፈፀም እንደ ባልና ሚስት የኖሩ ሲሆን ነው፡፡
9. **“የጋራ መኖሪያ ቦታ”** ማለት በዝምድና የተሳሰሩ ወይም በዝምድና ያልተሳሰሩ ሰዎች በጋራ የሚኖሩበት ስፍራ ነው፡፡
10. **“የጤና ተቋም”** ማለት የመንግስት፣ መንግስትዊ ያልሆነ እና የግል ሆስፒታሎች፣ ጤና ጣቢያዎች ፣ጤና ኬላዎችና ክሊኒኮችን ያጠቃልላል፡፡
11. **“ማዕረግ”** ማለት በመከላከያ፣ በፖሊስ፣ በዩኒቨርስቲ፣በሃይማኖት ተቋም፣ በውጭ ጉዳይ የሚሰጡ የክብር ስሞችን፣ ማዕረግ የመስጠት መብት ባላቸው ሌሎች አካላት የተሰጠ ማዕረግን እና የመሳሰሉትን ያጠቃልላል፡፡
12. **“መረጃ”** ማለት በወሳኝ ኩነት ምዝገባ ስርዓት የሚፈጠር የክብር መዝገብ ቅጂ፣ በኤሌክትሮኒክስ የሚደራጅ ፋይል፣ ሃርድ ኮፒ፣ የተጠቃለለና የተጠናቀረ መረጃን የሚያካትት ነው፣
13. **“ማስረጃ”** ማለት ከወሳኝ ኩነት ምዝገባ የሚመነጩ መረጃዎች የያዘና በህግ ለተፈቀደላቸው አካላት የሚሰጥ ሰነድ ነው።
14. **“የውጭ ዜጋ ”** ማለት ኢትዮጵያዊ ያልሆነ ማንኛውም ሰው ነው።
15. **“የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆነ የውጭ ዜጋ”** ማለት የሌላ ሀገር ዜግነት ከመያዙ አስቀድሞ የኢትዮጵያ ዜግነት የነበረው ወይም ከወላጆቹ፣ ከአያቶቹ ወይም ከቅድመ አያቶቹ ቢያንስ አንዱ በማናቸውም ጊዜ የኢትዮጵያ ዜግነት ይዞ የነበረ የውጭ ዜጋ ሲሆን፣ የኢትዮጵያን ዜግነት በመተው የኤርትራ ዜግነትን መርጦ የያዘ ሰውን አይጨምርም።
16. **“የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆነ የውጭ ዜጋ መታወቂያ ካርድ”** ማለት ለኢትዮጵያ ተወላጅ ለሆነ የውጭ አገር ዜጋ ወይም በልዩ ሁኔታ ለተፈቀደላቸው የሚሰጥ መታወቂያ ካርድ ነው።
17. **“ተተኪ የክብር መዝገብ ሹም”** ማለት የክልልና የፌዴራል ወሳኝ ኩነት መዝጋቢ ተቋማት በህግ በሚወስኑት መሰረት የክብር መዝገብ ሹሙን ተክቶ የወሳኝ ኩነት ምዝገባን የሚያከናውን ሰው ነው።
18. **“አዋጅ”** ማለት የወሳኝ ኩነት ምዝገባ እና ብሔራዊ መታወቂያ አዋጅ ቁጥር 760/2004 እና ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 1049/2009 ነው።
19. በአዋጁና በደንቡ ትርጓሜ የተሰጣቸው ቃላትና ሀረጎች በዚህ መመሪያ ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ።

## ክፍል ሁለት

## የወል ድንጋጌ

### 3. የምዝገባ አፈጻጸምና መረጃ አያያዝ መርሆዎች

1. በዚህ መመሪያ ተለይተው ከተመላከቱት መረጃዎች በስተቀር ሌላ ማንኛውንም ቃል በክብር መዝገብ ቅጾችና ቅጂዎች ላይ መጻፍ የተከለከለ ነው፡፡

2.ችሎታ የሌላቸው ግለሰቦች ላይ የሚከሰት የወሳኝ ኩነት ምዝገባ በተንከባካቢዎቻቸው ወይም በአሳዳሪዎቻቸው አማካኝነት ይሆናል፡፡ ሆኖም ግለሰቡ ችሎታ የሌለው መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ ከፍርድ ቤት መቅረብ አለበት፡፡

3. ትውልደ ኢትዮጵያዊ የሆኑ የውጭ ዜጎች ምዝገባ ቦታ በሁሉም ክልል በሚገኙ ዝቅተኛው የአስተዳደር ምዝገባ ጽህፈት ቤቶች ምዝገባው ይከናወናል፡፡

4. መረጃዎች ደህንነታቸው ተጠብቆ መያዝ አለባቸው፡፡

5. ከውጭ አገር ወደ ኢትዮጵያ የገቡ የኩነት ምዝገባ ደጋፊ ሰነዶች በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ካልተረጋገጠ እና በኢትዮጵያ የሰነዶች ማረጋገጠና ምዝገባ ኤጀንሲ ካልተመዘገበ በስተቀር ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

6. ክብር መዝገብ ሹሙ ምዝገባን ካጠናቀቀ በኋላ የአስተዳደር ጽህፈት ቤቱን ማህተም ማሳረፍ ያለበት ሲሆን የወሳኝ ኩነት መዋቅር በተዘረጋባቸው የአስተዳደር ጽህፈት ቤት የራሱን ማህትም መጠቀም አለበት፡፡

7. ኩነቱ የተከሰተው በክብር መዝገብ ሹሙ/ሟ ወይም በሚስቱ/በባሏ ወይም በወላጆቹ ወይም በተወላጆቹ ላይ ከሆነ ምዝገባው በተተኪ የክብር መዝገብ ሹም ይከናወናል፡፡

8. የክብር መዝገብ ሹሙ በሃላፊነት የተረከባቸውን የወሳኝ ኩነት ምዝገባ የክብር መዝገብ፣ የምስክር ወረቀትና ሌሎች ቁሳቁሶች ያለ በቂ ምክንያት ቢያጎድል አግባብ ባለው ህግ መሰረት ይጠየቃል፡፡

9. በምስክር ወረቀት ህትመት ወቅት ሴሪ/ተከታታይ/ ቁጥር ተካቶ መታተም አለበት፡፡

10. በወሳኝ ኩነት ምዝገባ አዋጅ 760/2004 እና 1049/2009 እንዲሁም በሌሎች ህግች ላይ ያሉ ድንጋጌዎች በዚህ መመሪያ ውስጥ የሌሉ በመሆናቸው በምዝገባ ወቅት አዋጁንና ሌሎች ህጎችን በማገናዘብ ምዝገባው የሚካሄድ ይሆናል።

## 4. ትውልደ ኢትዮጵያዊ ያልሆኑ የውጭ ዜጎች ወሳኝ ኩነት ምዝገባ ቦታ

ትውልደ ኢትዮጵያዊ ያልሆኑ የውጭ ዜጎች የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ቦታ በሁሉም ክልል በሚገኙ የዞኖች ከተማ ያለበት ዝቅተኛው አስተዳር ጽህፈት ቤት ይሆናል፡፡

## 5. መታወቂያን በበተመለከተ

1. የወሳኝ ኩነት አስመዝጋቢ ወይም ተመዝጋቢ ጊዜው ያላለፈበት የነዋሪነት ወይም ብሔራዊ መታወቂያ ወይም ከዝቅተኛው የአስተዳር አስተዳደር ጽህፈት ቤት መደበኛ ነዋሪነቱን የሚገልጽ የድጋፍ ደብዳቤ ወይም ስደተኛነቱን የሚገልጽ ማስረጃ ወይም የመኖሪያ ፍቃድ ወይም ከሚሰራበት መስሪያ ቤት ባልደረባነቱን እና ዜግነቱን የሚገልጽ የድጋፍ ደብዳቤና የመስሪያ ቤቱን መታወቂያ ወይም የመከላከያ ሰራዊት መታወቂያ ማቅረብ አለበት፡፡
2. ካምፐ/ፕሮጄክት በሚገኝበት አስተዳደር ጽ/ቤት መደበኛ ነዋሪነት መታወቂያ የሌላቸዉ አስመዝጋቢዎችና ተመዝጋቢዎች ወሳኝ ኩነት ማስመዘገብ ወይም መመዝገብ ሲፈልጉ ካምፑ/ ፕሮጄክቱ/ ፋብሪካው የአስተዳር አስተዳደር ጽህፈት ቤት በሚገኝበት አስተዳደር ጽ/ቤት አካባቢ መሆናቸውን በማረጋገጥና ተመዝጋቢዎቹ ወይም አስመዝጋቢዎቹ የካምፑ/ የፕሮጄክቱ/ የፋብሪካው ሰራተኛ መሆናቸውን የሚገልጽ ማስረጃ ማቅረብ አለባቸው፡፡

## 6. የምዝገባ ቦታ

### 1. ክልል

ምዝገባው የሚካሄደበት አስተዳደር ጽህፈት ቤት  የሚገኝበት ክልል ስም ይመዘገባል፡፡

### 2. ዞን/ከተማ አስተዳደር

ምዝገባው የሚካሄደበት አስተዳደር ጽህፈት ቤት የሚገኝበት ዞን/ከተማ አስተዳደር ስም/ቁጥር ይመዘገባል፡፡ ከተማ አስተዳደር ሲባል በዞን አስተዳደር ደረጃ የሚገኙ ከተሞች ናቸው፡፡

### 3. ከተማ

ምዝገባው የሚካሄድበት አስተዳደር ጽህፈት ቤት የሚገኝበት ከተማ ስም ይመዘገባል፡፡ የገጠር ቀበሌ ከሆነ በሰረዝ ምልክት (-) ይታለፋል፡፡

### 4. ክፍለ ከተማ

ምዝገባው የሚካሄድበት አስተዳደር ጽህፈት ቤት የሚገኝበት ክፍለ ከተማ ስም/ቁጥር ይመዘገባል፡፡

### 5. ወረዳ/ልዩ ወረዳ

ምዝገባው የሚካሄድበት አስተዳደር ጽህፈት ቤት የሚገኝበት ወረዳ/ልዩ ወረዳ/ከተማ አስተዳደር ስም/ቁጥር ይመዘገባል፡፡

### 6. ቀበሌ

ምዝገባው የሚካሄድበት አስተዳደር ጽህፈት ቤት ስም/ቁጥር ይመዘገባል፡፡

## 7. ዜግነት

ዜግነት ከነዋሪነት/ብሔራዊ መታወቂያ ወይም ከፓስፖርት ወይም ከትውልደ ኢትዮጵያዊነት መታወቂያ ወይም ከመኖሪያ ፈቃድ ላይ በማየት ይመዘገባል፡፡

### 8. የነዋሪነት/ብሔራዊ መታወቂያ ቁጥር

የነዋሪነት ወይም ብሔራዊ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ወይም ትውለደ ኢትዮጵያዊ መታወቂያ ቁጥር ከነዋሪነት/ብሔራዊ/ፓስፖርት/ ትውለደ ኢትዮጵያዊ መታወቂያ ላይ በመውሰድ ይመዘገባል፡፡

### 9. የትውልድ ወር፣ ቀን እና ዓመተ ምህረት

የትውልድ ወር ስም በፊደል፣ ቀን በሁለት አሀዝ ሆኖ በቁጥር እና ዓመተ ምህረት በአራት አሀዝ ሆኖ በቁጥር ይመዘገባል፡፡

### 10. የትውልድ ቦታ/ሀገር

የትውልድ ቦታ የዞን/በዞን ደረጃ ያለ ክፍለ ከተማ እና የወረዳ/ልዩ ወረዳ ስም/ቁጥር ወይም በወረዳ ደረጃ ያለ ክፍለ ከተማ ይመዘገባል፡፡ የትውልድ ሀገር ከኢትዮጵያ ውጭ ከሆነ የሀገሩ ስም ይመዘገባል፡፡

### 11. መደበኛ መኖሪያ ቦታ/ሀገር

በምዝገባ ወቅት አስመዝጋቢዎች/ተመዝጋቢዎች የሚገኙበት ክልል፣ ዞን/ከተማ አስተዳደር፣ ከተማ፣ ክፍለ ከተማ፣ ወረዳ/ልዩ ወረዳ እና ቀበሌ ስም/ቁጥር ይመዘገባል፡፡ የመደበኛ መኖሪያ ሀገር ከኢትዮጵያ ውጭ ከሆነ የሀገሩ ስም ይመዘገባል፡፡

### 12. የጋብቻ ሁኔታ

ኩነቱ በተከሰተበት ወቅት አስመዝጋቢዎች/ተመዝጋቢዎች የነበራቸው የጋብቻ ሁኔታ በመጠየቅ ያገቡ ከሆነ **"ያገባች/ያገባ"**፣ ያላገቡ ከሆነ **"ያላገባች/ያላገባ"**፣ የተፋቱ ከሆነ **"የተፋታች/የተፋታ"**፣ ከቀድሞ

ጋብቻ በሞት የተለያዩ ከሆነ **"የሞተባት/የሞተችበት"** ወይም ጋብቻ ሳይፈፅሙ እንደባልና ሚስት የሚኖሩ ከሆነ **"እንደባልና ሚስት የምትኖር/የምኖር"** ተብሎ ይመዘገባል፡፡

## 13. ሃይማኖት

አስመዝጋቢው/ተመዝጋቢው የሚከተለው እምነት ወይም ሃይማኖት ተጠይቆ ይመዘገባል፡፡ ሀይማኖት የለኝም ካለ "**የሌላት/የሌለው**" ተብሎ ይመዘገባል፡፡

## 14. ብሔር

1. የአስመዝጋቢው/ተመዝጋቢው ኢትዮጵያዊ ከሆኑ ብሔር ተጠይቆ ከብሔር መጠሪያ ዝርዝር አባሪ ቁጥር 01 ጋር ተገናዝቦ ይመዘገባል፡፡
2. የአስመዝጋቢው/ተመዝጋቢው የውጭ አገር ዜጎች ከሆኑ ብሔር የአስመዝጋቢው ወይም የተመዝጋቢው አገር ስም ይመዘገባል፡፡

## 15. የትምህርት ሁኔታ

አስመዝጋቢዎች/ተመዝጋቢዎች ኩነቱ በተከሰተበት ወቅት የማንበብና መጻፍ ሁኔታ ወይም ያጠናቀቁት ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ ተጠይቆ ከትምህርት ደረጃ ዝርዝር አባሪ ቁጥር 02 ጋር ተገናዝቦ ይመዘገባል፡፡

## 16. የስራ ዓይነት

አስመዝጋቢዎች/ተመዝጋቢዎች ኩነቱ በተከሰተበት ወቅት በመደበኛነት የሚሰሩት የሥራ ዓይነት በመጠየቅ ይመዘገባል፡፡ ከአንድ በላይ የስራ አይነት ያላቸው ከሆነ አብዛኛው ጊዜያቸውን የሚያጠፋበት የስራ አይነት ተጠይቆ ይመዘገባል፡፡

## 17. ፊርማ

1. ማንኛውም ፊርማ በጽሁፍ መፈረም አለበት፣
2. በጽሁፍ መፈረም የማይችል ሰው በጣት አሻራው መፈረም አለበት፤
3. በጣት አሻራ መፈረም የማይችል ከሆነ ይኸው ተገልጾ ምስክር ባለበት የክብር መዝገብ ሹሙ ይፈርማል፤

## 18. የክብር መዝገብ ሹሙን በተመለከተ

### 1. ስም፣ የአባት ስም፣ የአያት ስም

ስም፣ የአባት ስምና የአያት ስም በቅደም ተከተላቸው ይመዘገባል፡፡

### 2. የተመዘገበበት ወር፣ ቀን እና ዓመተ ምህረት

ልደት የተመዘገበበት ወር ስም በፊደል፣ ቀን በሁለት አሀዝ ሆኖ በቁጥር እና ዓመተ ምህረት በአራት አሀዝ ሆኖ በቁጥር ይመዘገባል፡፡

### 3. ፊርማ

የክብር መዝገብ ሹሙ ፊርማውን ይፈርማል፡፡

# ክፍል ሦስት

# የልደት ምዝገባ

## ንዑስ ክፍል አንድ

## በልደት ምዝገባ ወቅት መሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎችና ደጋፊ ማስረጃዎች

## 19. ቅድመ ሁኔታዎች

1. የህፃኑ ወላጆች በህይወት ካሉ አባት እና እናት ሁለቱም ወይም ልደትን ለማስመዝገብ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ተገኝቶ ልደቱን ማስመዝገብ ያልቻለው ወላጅ አባት ከሆነ ለህፃኑ ወላጅ እናት ልዩ የልደት ውክልና በመስጠት እንዲሁም ተገኝታ ማስመዝገብ ያልቻለችው ወላጅ እናት ከሆነች ለህፃኑ ወላጅ አባት ልዩ የልደት ውክልና በመሰጠት ልደትን ማስመዝገብ ይቻላሉ፡፡

2. ከወላጆቹ አንዱ በህይወት የሌለ እንደሆነ በህይወት ያለው ወላጅ የሟች ወላጅን ህጋዊ የሞት ማስረጃ ሲያቀርብ ልደቱ ይመዘገባል።
3. ችሎታ የሌላቸው ሰዎች በተንከባካቢዎቻቸው ወይም በአሳዳሪዎቻቸው አማካይነት መመዝገብ ይችላሉ።
4. ልደት የሚመዘገበው በህይወት ለተወለደ ወይም በሕይወት ተወልዶ ወዲያውኑ ለሞተ ሲሆን ሞቶ የተወለደ ከሆነ ግን አይመዘገብም፡፡
5. ዕድሜው 18 ዓመትና በላይ የሆነ ልደት ምዝገባ አገልግሎት ፈላጊ ልደቱን ራሱ ማስመዝገብ አለበት።

6. 18 ዓመት ሳይሞላቸው ልጅ የወለዱ ወላጆች የልጃቸውን ልደት ለማስመዝገብ ሲቀርቡ ከሚኖሩበት መደበኛ መኖሪያ ቦታ ካለው ዝቅተኛ አስተዳደር ጽህፈት ቤት ማንነታቸውን የሚገልጽ የድጋፍ ደብዳቤ በማቅረብ ልደቱን ማስመዝገብ ይችላሉ።
7. ልደት ተመዝጋቢው የውጭ ዜጋ ከሆነ በኢትዮጵያ ውስጥ የተወለደ መሆን አለበት፡፡
8. ዕድሜው 18 ዓመትና በላይ የሆነ ልደት ተመዝጋቢ ወላጆቹን በሚመለከት ቦታ ላይ መረጃውን ካስሞላ በኋላ የወላጅ ፊርማ ቦታ ላይ ሰረዝ (-) ምልክት በማድረግ ይታለፋል።

## 20. ደጋፊ ማስረጃዎች

1. ልደቱ የተከሰተው በጤና ተቋም ከሆነ አስመዝጋቢው ከጤና ተቋም የተሰጠውን የልደት ማሳወቂያ ቅጽ ማቅረብ አለበት፡፡
2. የህጻኑ አሳዳሪ ወይም ተንከባካቢ ልደቱን ለማስመዝገብ ሲቀርብ ከፍርድ ቤት የተሰጠ የአሳዳሪነት ወይም የተንከባካቢነት ሕጋዊ ማስረጃ ማቅረብ አለባቸው፡፡
3. ተጥሎ የተገኘ ህፃንን ለማስመዝገብ የሚመጣ ፖሊስ ወይም አግባብ ያለው የመንግስት አካል ማንነቱን የሚገልጽ ሕጋዊ መታወቂያ ወይም ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡
4. የልደት ተመዝጋቢው የውጭ ዜጋ ከሆነ ከጤና ተቋም የተሰጠ ማስረጃ መቅረብ አለበት፡፡

# ንዑስ ክፍል ሁለት

# መለያ ቁጥር

## 21. የልደት ክብር መዝገብ ቅጽ ቁጥር

የልደት ክብር መዝገብ ቅጽ ቁጥር በህትመት ወቅት ለቅጹ የተሰጠ ቁጥር ነው፡፡

## 22. የምዝገባ ጽህፈት ቤት መለያ ቁጥር

ኤጀንሲው አግባብ ካለው የክልል አካል ጋር በመተባበር በሚያወጣው ዝርዝር ኮድ መሰረት ይመዘገባል፡፡

## 23. የልደት ምዝገባ ልዩ መለያ ቁጥር

ከላይ በአንቀጽ 22 ስር የተመዘገበውን የምዝገባ ጽህፈት ቤት መለያ ቁጥር፣ የምዝገባው ዓመተ ምህረት በአራት አሀዝ ሆኖ በቁጥር እና የልደቱን መለያ ተራ ቁጥር በአራት አሀዝ ሆኖ በቁጥር ቅደም ተከተል ይመዘገባል፡፡

## ንዑስ ክፍል ሦስት

## ህጻኑን/ኗን በተመለከተ

### 24. ስም፣ የአባት ስም እና የአያት ስም

1. በዚህ ክፍል ለህፃኑ የተሰጠው የግል ስም፣ የወላጅ አባት ስም እና የአያት ስም ይመዘገባል፡፡
2. ልደት ሲመዘገብ የህፃኑ አባት ያልታወቀ እንደሆነ የእናትየዋ አባት ስም የልጁ አባት ስም ሲሆን የእናትየዋ አያት ስም ደግሞ የልጁ አያት ስም ሆኖ ይመዘገባል፡፡

### 25. ጾታ

የህጻኑ ጾታ ከአስመዝጋቢው ተጠይቆ "ወንድ" ወይም "ሴት" ተብሎ ይመዘገባል፡፡

### 26. ዜግነት

1. የህፃኑ ዜግነት ከወላጆቹ ተጠይቆ ይመዘገባል፡፡
2. ከወላጆቹ አንዱ የውጪ አገር ዜጋ ከሆነ የህፃኑ ዜግነት በኢትዮጵያዊ ወላጅ ውሳኔ መሰረት ይመዘገባል፡፡

### 27. የተወለደበት/ችበት ወር፣ ቀን እና ዓመተ ምህረት

1. ልደቱ የተከሰተበትን ወር ስም በፊደል፣ የቀን ስም በሁለት አሀዝ ሆኖ በቁጥር እና ዓመተ ምህረት በአራት አሀዝ ሆኖ በቁጥር ከጤና ተቋም/መዋቅር ከተሰጠ የልደት ማሳወቂያ ቅጽ ላይ በመውሰድ ይመዘገባል፡፡ ሆኖም ያልተሟላ መረጃ ካጋጠመ ወይም ከጤና ተቋም የልደት ማሳወቂያ ምስክር ወረቀት ካልመጣ አስመዝጋቢውን በመጠየቅ ይመዘገባል፡፡

### 28. ልደቱ የተከሰተበት ሥፍራ/ተቋም አይነትና የተሰጠ ማስረጃ ካለ የማስረጃው ቁጥር

1. ህጻኑ የተወለደው በጤና ተቋም ከሆነ የተቋሙ ስም፣ ዓይነት (ሆስፒታል /ጤና ጣቢያ/ ክሊኒክ/ጤና ኬላ) እና ባለቤትነት (የመንግስት/መንግስታዊ ያልሆነ እና የግል) ለአስመዝጋቢው ከተሰጠው ማሳወቂያ ቅጽ ላይ ተወስዶ ይመዘገባል፡፡
2. ከህክምና ተቋማት የተሰጠ ማስረጃ የማስረጃው ቁጥር ለአስመዝጋቢው ከተሰጠው የማሳወቂያ ቅጽ ላይ በመውሰድ ይመዘገባል፡፡
3. ህፃኑ የተወለደው ከጤና መዋቅር ውጭ ከሆነ የተወለደበት ስፍራ (በቤት/ጎዳና/ህፃናት ማሳደጊያ/ማረሚያ ቤትና የመሳሰሉት) ስም ይመዘገባል፡፡

## 29. የትውልድ ቦታ

ህፃኑ የተወለደበት ስፍራ ወይም ተቋም የሚገኝበት ክልል፣ ዞን/ከተማ አስተዳደር፣ ከተማ፣ ክፍለ ከተማ፣ ወረዳ/ልዩ ወረዳ ቀበሌ ስም/ቁጥር ይመዘገባል፡፡

## 30. የልደቱ አይነት

ልደቱ አንድ ከሆነ "ነጠላ"፣ ሁለት ከሆነ "መንታ" እና ከሁለት በላይ ከሆነ የልደቱ ብዛት በፊደል ይመዘገባል፡፡ የልደቱ ዓይነት ከአንድ በላይ ከሆነ እንደ ልደቱ ብዛት በተለያየ የልደት ክብር መዝገብ ቅጽ ላይ ይመዘገባል፡፡

## 31. በልደት ጊዜ የተደረገ ዕርዳታ

ልደቱ የተከሰተው በጤና ተቋም ከሆነ የጤና ተቋሙ ከሰጠው ማስረጃ ላይ በልደት ጊዜ የተደረገ እርዳታን በማየት ይመዘገባል፡፡ በልደት ጊዜ የተደረገ እርዳታ ከሌለ የሰረዝ ምልክት (-) በማድረግ ይመዘገባል፡፡

## 32. ክብደት በልደት ወቅት

የህጻኑ ክብደት የሚመዘገበው ከጤና ተቋም ከሚመጣ የልደት ማሳወቂያ ማስረጃ ላይ በመውሰድ ብቻ ነው፡፡ ማስረጃው ላይ የተመዘገበው የክብደት መጠን በግራም ተሞልቶ መምጣት ያለበት ሲሆን ሆኖም በኪሎ ግራም ተሞልቶ ከመጣ የክብር መዝገብ ሹሙ ወደ ግራም በመለወጥ ይመዘግባል፡፡ (1 ኪሎ ግራም =1,000 ግራም) የህፃኑ ክብደት መረጃ ያልተገኘ ከሆነ (-) ምልክት በማድረግ ይመዘገባል፡፡

## 33. ያዋለደው/ችው የሙያ ደረጃ

እናትየዋን በወሊድ ወቅት በህክምና ተቋም ወይም በልምድ አዋላጅ መውለዷን ከህክምና ተቋሙ ከመጣ ማስረጃ ላይ በማየት የባለሙያውን የሙያ ደረጃ ወይም በልምድ አዋላጅ በማለት ይመዘገባል፡፡

# ንዑስ ክፍል አራት

# ወላጅ እናትንና አባትን በተመለከተ

## 34. ስም፣ የአባት ስም እና የአያት ስም

1. በቅደም ተከተላቸው ከነዋሪነት/ብሔራዊ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ላይ በማየት ይመዘገባል፡፡
2. በፓስፖርት ላይ የግልና የአባት ስም ወይም የግልና የአያት ስም ብቻ ሆኖ ሲገኝ በፓስፖርቱ ላይ ያለው ብቻ ተወስዶ የሚመዘገብ ሲሆን ያልተገለጸው ስም በሰረዝ (-) ይታለፋል፡፡

## ንዑስ ክፍል አምስት

## አስመዝጋቢን በተመለከተ /አስመዝጋቢው ከወላጅ እናት ወይም አባት ውጭ ከሆነ ብቻ የሚሞላ

### 35. ስም፣ የአባት ስም፣ የአያት ስም

ስም፣ የአባት ስም እና የአያት ስም በቅደም ተከተል ይመዘገባል።

### 36. ፆታ

ፆታ "ወንድ" ወይም "ሴት" ተብሎ ይመዘገባል።

### 37. ከህጻኑ/ኗ ጋር ያለው/ያላት ዝምድና

አስመዝጋቢው ከተመዝጋቢው ጋር ያለው የዝምድና ዓይነት ተጠይቆ ይመዘገባል። ዝምድና የሌለው ከሆነ የሌለው ተብሎ ይሞላል።

## ክፍል አራት

## የጉዲፈቻ ምዝገባ

## ንዑስ ክፍል አንድ

## በጉዲፈቻ ምዝገባ ወቅት መሟላት የሚገባቸው ደጋፊ ማስረጃዎች

### 38. ደጋፊ ማስረጃዎች

1. ጉዲፈቻ የተደረገው ልጅ የቀድሞ የልደት ምስክር ወረቀት ካለው ለምዝገባው ሂደት የሚያስፈልጉ መረጃዎች ከምስክር ወረቀቱ ከተወሰዱ በኂላ ለክብር መዝገብ ሹሙ መመለስ አለበት፣
2. በፍርድ ቤት የፀደቀ የጉዲፈቻ ስምምነት ትክክለኛ ግልባጭ መቅረብ አለበት።
3. የጉዲፈቻ አድራጊዎች የጋብቻ ሁኔታ የሚገልፅ ማስረጃ መቅረብ አለበት።

## የጉዲፈቻ ክብር መዝገብ ቅጽ ዝርዝር መረጃ አመዘጋገብ

## ንዑስ ክፍል ሁለት

## መለያ ቁጥር

### 39. የጉዲፈቻ ክብር መዝገብ ቅጽ ቁጥር

የጉዲፈቻ ክብር መዝገብ ቅጽ ቁጥር በህትመት ወቅት ለቅጹ የተሰጠ ቁጥር ነው።

### 40. የምዝገባ ጽ/ቤት መለያ ቁጥር

ኤጀንሲው አግባብ ካለው የክልል አካል ጋር በመተባበር በሚያወጣው ዝርዝር ኮድ መሰረት ይመዘገባል፡፡

## 41. የጉዲፈቻ ምዝገባ ልዩ መለያ ቁጥር

ከላይ በአንቀጽ 40 ላይ የተመለከተውን የምዝገባ ጽህፈት ቤት መለያ ቁጥር፣ የምዝገባው ዓመተ ምህረት በአራት አሀዝ ሆኖ በቁጥር እና የጉዲፈቻው መለያ ተራ ቁጥር በአራት አሀዝ ሆኖ በቁጥር ቅደም ተከተል ይመዘገባል፡፡

## 42. የልደት ምዝገባ ልዩ መለያ ቁጥር

ልደቱ በአዋጅ ቁጥር 760/2004 መሠረት የተመዘገበ ከሆነ የጉዲፈቻ ተደራጊን የልደት ምዝገባ ልዩ መለያ ቁጥር ከምስክር ወረቀት ላይ በመውሰድ ይመዘገባል፡፡ ሆኖም በቀድሞው ህጎችና ልማዳዊ አሰራሮች መሰረት የተሰጠ ከሆነ የልደት ምስክር ወረቀት መለያ ቁጥር ወይም የክብር መዝገብ መለያ ቁጥር ይመዘገባል፡፡

## ንዑስ ክፍል ሦስት

## የጉዲፈቻ ልጅን በተመለከተ

## 43. ስም፣ የአባት ስም እና የአያት ስም

1. ጉዲፈቻ አድራጊዎች ባለትዳር ከሆኑ የጉዲፈቻ ልጅ ስም ከጉዲፈቻ ውል ላይ የተፃፈው ስም፣ የአባት ስም የጉዲፈቻ አድራጊው ስም ሲሆን የአያት ስም የጉዲፈቻ አድራጊው አባት ስም ይመዘገባል፡፡
2. ጉዲፈቻ አድራጊው ወንድ ከሆነ የጉዲፈቻ ልጅ ስም ከጉዲፈቻ ውል ላይ የተፃፈውን በመውሰድ የጉዲፈቻ አድራጊው ስም የጉዲፈቻ ተደራጊው ልጅ አባት ስም ሲሆን የጉዲፈቻ አድራጊው አባት ስም የጉዲፈቻ ተደራጊው ልጅ አያት ስም ሆኖ ይመዘገባል፡፡
3. ጉዲፈቻ አድራጊዋ ሴት ከሆነች የጉዲፈቻ ልጅ ስም ከጉዲፈቻ ውል ላይ የተፃፈው ስም፣ የአባት ስም የጉዲፈቻ አድራጊዋ አባት ስም እና የአያት ስም የጉዲፈቻ አድራጊዋ አያት ስም ይመዘገባል፡፡

## 44. ጾታ

የጉዲፈቻ ልጅ ጾታ በፍርድ ቤት ከፀደቀው የውል ስምምነት ላይ በመውሰድ “ወንድ” ወይም “ሴት” ተብሎ ይመዘገባል፡፡

## 45. የትውልድ ወር፣ ቀን እና ዓመተ ምህረት

ጉዲፈቻ ተደራጊው ልጅ የትውልድ ዘመን ከልደት የምስክር ወረቀት በማየትና የልደት ምስክር ወረቀቱ ላይ በተፃፈው አግባብ መሰረት ይመዘገባል፡፡ ሆኖም የልደት ምስክር ወረቀት ከሌለ ጉዲፈቻ አድራጊውን በመጠየቅ ይመዘገባል፡፡

## 46. የትውልድ ቦታ

የጉዲፈቻ ልጅ ትውልድ ቦታ ክልል፣ ዞን/ከተማ አስተዳደር፣ ከተማ፣ ክፍለ ከተማ፣ ወረዳ/ልዩ ወረዳ/ቁጥር ቀበሌ/ቁጥር ስም ይመዘገባል፡፡

## 47. መደበኛ መኖሪያ ቦታ

የጉዲፈቻ ልጅ መደበኛ መኖሪያ ቦታ ጉዲፈቻ ከመደረጉ በፊት ወላጆቹ/ጉዲፈቻ ሰጭዎች በስምምነቱ ጊዜ የሚኖሩበት ክልል፣ ዞን/ከተማ አስተዳደር፣ ከተማ፣ ክፍለ ከተማ፣ ወረዳ/ልዩ ወረዳ፣ የቀበሌ ስም/ቁጥርና የቤት ቁጥር ይመዘገባል፡፡

## 48.የትምህርት ሁኔታ

ጉዲፈቻ ተደራጊው ልጅ የትምህርት ሁኔታ ጉዲፈቻው በፀደቀበት ወቅት ያጠናቀቀው ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ ተጠይቆ ከትምህርት ደረጃ ዝርዝር አባሪ ቁጥር 02 ጋር ተገናዝቦ ይመዘገባል፡፡

## 49. ለጉዲፈቻ የተሰጠበት ምክንያት

በፍርድ ቤት የፀደቀውን የጉዲፈቻ ስምምነት በማየት ይመዘገባል፡፡ ስምምነቱ ላይ ጉዲፈቻ የተሰጠበት ምክንያት ካልተጠቀሰ በሰረዝ ምልክት (-) ይታለፋል፡፡

# ንዑስ ክፍል አራት

# ጉዲፈቻ አድራጊን በተመለከተ

## 50. ስም፣ የአባት ስም እና የአያት ስም

የጉዲፈቻ አድራጊ ስም፣ የአባት ስም እና የአያት ስም በፍርድ ቤት ከፀደቀ ውሳኔ ላይ በማየት ይመዘገባል፡፡

## 51. ዜግነት

የጉዲፈቻ አድራጊ ዜግነት በፍርድ ቤት ከፀደቀ ውሳኔ ከነዋሪነት ወይም ብሄራዊ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ላይ በመውሰድ ይመዘገባል፡፡

## ንዑስ ክፍል አምስት

## በፍርድ ቤት የፀደቀውን የጉዲፈቻ ስምምነት በተመለከተ

## 52. ያፀደቀው ፍርድ ቤት ስም እና አድራሻ

በፍርድ ቤት ከፀደቀው የጉዲፈቻ ስምምነት ግልባጭ በማየት ይመዘገባል፡፡

## 53. ጉዲፈቻ የፀደቀበት ወር ፣ቀን እና ዓመተ ምህረት

ፍርድ ቤቱ የጉዲፈቻውን ስምምነት ያፀደቀበትን ወር ፣ቀን እና ዓመተ ምህረት ፍርድ ቤት ከፀደቀው ስምምነት ግልባጭ በማየት የሚመዘገብ ሲሆን የወር ስም በፊደል፣ ቀን በሁለት አሀዝ ሆኖ በቁጥር እና ዓመተ ምህረት በአራት አሀዝ ሆኖ በቁጥር ይመዘገባል፡፡

## 54. የፍርድ ቤት መዝገብ ቁጥር

የፍርድ ቤት መዝገብ ቁጥር ከፀደቀው የጉዲፈቻ ስምምነት ግልባጭ በማየት ይመዘገባል፡፡

## ክፍል አምስት

## አባትነትን በፍርድ ቤት ማወቅ እና ልጅነትን መቀበል ምዝገባ

## ንዑስ ክፍል አንድ

## አባትነትን በፍርድ ቤት ማወቅ

## 55. ደጋፊ ማስረጃዎች

1. የአስመዝጋቢው የነዋሪነት/ብሔራዊ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ይዞ መቅረብ አለበት፡፡
2. አስመዝጋቢ የፍርድ ቤት ውሳኔ ይዞ መቅረብ አለበት፡፡

## 56. አባትነትን በፍርድ ቤት ማወቅ ምዝገባ

1. የህፃኑ ልደት ተመዝግቦ የነበረ ከሆነ የአባትነትን በፍርድ ቤት ማወቅ ውሳኔን መሠረት አድርጎ የህፃኑ ወላጅ አባትና አያት በሚመለከት ቀድሞ የተመዘገበው መረጃ በፍርድ ቤት ውሳኔ መሰረት ይመዘገባል፡፡

2. የህፃኑ ልደት ቀደም ሲል በክብር መዝገብ ያልተመዘገበ ከሆነ ልደቱ በልደት አመዘጋገብ መመሪያ መሰረት ይመዘገባል፡፡

## ንዑስ ክፍል ሁለት

## ልጅነትን መቀበል

### 57. ቅደመ ሁኔታ

1. አባት የክብር መዝገብ ሹም ፊት ቀርቦ ልጄ ነው ብሎ ቃሉን መስጠት አለበት፡፡
2. በፍርድ ቤት የፀደቀ ኑዛዜ ሲቀርብና ከአባትየው ወላጆች አንዱ በወላጅ አባት ስም ልጁን ሲቀበሉ እና የልጁ እናት የተቀባዩን አባትነት አምና ስትቀበል ኩነቱ ይመዘገባል፡፡
3. ልጁ ለአካለ መጠን የደረሰ የሆነ እንደሆነ አባት ልጁን የመቀበሉ ተግባር የሚመዘገበው ልጁ አባትነቱን የተቀበለ እንደሆነ ነው፡፡
4. ወላጅ አባት አካለ መጠን ያልደረሰ ቢሆንም ልጄ ነው ሲል ቃል መስጠት የሚችለው አባት ብቻ ነው፡፡
5. በወኪል አማካይነት ቃሉን የሚሰጥ ከሆነ በፍርድ ቤት የጸደቀ ልዩ የውክልና ማስረጃ መቅረብ አለበት፡፡
6. የልጁ እናት የተቀባዩን አባትነት እውነትነት ያለው መሆኑን ካላመነች በስተቀር የክብር መዝገብ ሹሙ መመዝገብ የለበትም፡፡
7. የክብር መዝገብ ሹሙ ልጅነትን መቀበልን ለመመዝገብ አባት ጥያቄ ካቀረበበት ቀን ጀምሮ ለ30 ተከታታይ ቀናት የሚቆይ ማስታወቂያ በመለጠፍ ክርክር ያልተነሳ እንደሆነ ኩነቱን ይመዘግባል፡፡
8. የልጁ አባት የሞተ ወይም ፍቃዱን ለመስጠት የማይችል በሆነ ጊዜ ከአባትየው ወላጆች አንዱ በእርሱ ስም ልጄ ነው ሲል ለክብር መዝገብ ሹም ቃሉን ሊሰጥ ይችላል፡፡
9. የልጁ እናት የሞተች ወይም ፍቃዷን ለመግለጽ የማትችል ሆና የተገኘች እንደሆነ የእምነት ቃሉን ከልጁ እናት ወላጆች በአንደኛው ሊሰጥ ይችላል፡፡
10. የልጁ እናት ወላጆች በሌሉ ጊዜ ወደ ላይ በሚቆጠር ሌላ ወላጅ ወይም በፍርድ በተከለከለው ሰው አሳዳሪ የእምነት ቃሉ ሊሰጥ ይችላል፡፡
11. ልጅነትን በክብር መዝገብ ሹም ፊት የሚቀበል ሰው ሲቀርብ ከቀረበበት ቀን አንስቶ እስከ 30 ቀን ውስጥ ባለው ጊዜ ውስጥ የእኔ ልጅ ነው የሚል ተቃዉሞ ካልቀረበ ምዝገባው ይከናወናል፡፡

### 58. ደጋፊ ማስረጃ

አንድ ሰው የክብር መዝገብ ሹም ፊት በመቅረብ አባት መሆኑን በመግለጽ በሚሰጠው ቃል ወይም በጽሁፍ በሚያደርገው ኑዛዜ ወይም በሌላ በማናቸውም ሥልጣን በተሰጠው ባለሥልጣን በተረጋገጠ ሰነድ አማካኝነት አባት መሆኑን ማስመዝገብ ይችላል፡፡

## 59. ልጅነትን መቀበል አመዘጋገብ

1. የህፃኑ ልደት ተመዝግቦ የነበረ ከሆነ አባት በሰጠው ቃል ወይም በፍርድ ቤት በተረጋገጠ ኑዛዜ መሠረት አድርጎ የህፃኑ ወላጅ አባትና አያት በሚመለከት ቀድሞ የተመዘገበው መረጃ በአዲሱ ይተካል፡፡
2. የህፃኑ ልደት ቀደም ሲል በክብር መዝገብ ያልተመዘገበ በዚህ መመሪያ ክፍል ሦስት መሰረት ይመዘገባል፡፡

# ክፍል ስድስት

# የጋብቻ ምዝገባ

## ንዑስ ክፍል አንድ

## ለጋብቻ ምዝገባ የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች፣ ደጋፊ ማስረጃዎችና የጋብቻ አፈጻጸም ቅደም ተከተል

## 60. ቅድመ ሁኔታዎች

1. ተጋቢዎች ጋብቻ ለመፈፀም ማሰባቸውን እጅግ ቢዘገይ ጋብቻቸውን ለመፈፀም ከወሰኑበት ቀን ከአንድ ወር በፊት ለክብር መዝገብ ሹሙ ማስታወቅ አለባቸው፡፡ ሆኖም ይህ ድንጋጌ በሃይማኖታዊ እና ባህላዊ ስርዓት የሚፈፀም ጋብቻን አይመለከትም፡፡
2. የክብር መዝገብ ሹሙ ጥያቄው በቀረበለት ቀን ከተጋቢዎቹ ጋር በመነጋገር ከወሰነ በኋላ በማግስቱ ጋብቻው የሚፈፀምበትን ቀን በመግለጽ አመቺ በሆነው መንገድ ለ15 ተከታታይ ቀን የሚቆይ ማስታወቂያ ያወጣል፡፡
3. ማስታወቂያ ከተለጠፈበት ቀን ጀምሮ ባሉት ተከታታይ 15 ቀናት ውስጥ የጋብቻ መቃወሚያ በጽሁፍ መቅረብ አለበት፤ መቃወሚያ ሊያቀርቡ የሚችሉ ወላጆችና ተወላጆች፣ አቃቤ ሕግ፣ አሳዳሪ ወይም የቀደመ ጋብቻ አለኝ የሚል ሰው መሆን አለበት፡፡
4. የክብር መዝገብ ሹሙ በቀረበው የጋብቻ መቃወሚያ ላይ በአምስት ተከታታይ ቀናት ውስጥ ውሳኔ በመስጠት ማሳወቅ አለበት፡፡
5. ወንደም ሆነ ሴቷ 18 ዓመት ሳይሞላቸው ጋብቻ መፈፀም አይችለም፡፡
6. ከባድ ምክንያት ሲያጋጥም ተጋቢዎቹ ወይም ከተጋቢዎቹ የአንዳቸዉ ወላጆች ወይም አሳዳሪ በሚያቀርቡት ጥያቄ መሰረት ጠቅላይ ዐቃቤ ህጉ ከመደበኛ የጋብቻ ዕድሜ ከሁለት ዓመት ያልበለጠ ጊዜ በመቀነስ እንዲጋቡ መፍቀድ ይችላል፡፡
7. ጋብቻ ህግ በሚከለክላቸው የስጋና የጋብቻ ዘመዳሞች መካከል መፈፀም የተከለከለ ነው፡፡

8. ተጋቢዎች በፍርድ ቤት እንዳያገቡ የተከለከሉ መሆናቸውን የሚገልጽ የጽሁፍ ማስረጃ የተገኘ እንደሆነ የክብር መዝገብ ሹሙ ጋብቻውን አይመዘግብም፡፡
9. ማንኛዉም ጋብቻ በፌዴራል ወይም በክልል የቤተሰብ ህግ መሰረት ተፈፀሚ ይሆናል፡፡
10. በባህል ስርዓት መሰረት የሚፈፀም ጋብቻ አንድ ወንድና አንዲት ሴት በሚኖሩበት አካባቢ ባህል ወይም በሁለቱ ተጋቢዎች ወይም ከሁለቱ ተጋቢዎች በአንዳቸው ባህል መሰረት የተፈፀመ መሆን አለበት፡፡
11. አዋጅ 760/2004 ከመተግበሩ በፊት በባህላዊ ወይም በሃይማኖታዊ ጋብቻ ስርዓት ተጋብተው ማስረጃ የጠፋባቸው ተጋቢዎች ስለጋብቻው የሚያውቁ በባል በኩል 2 በሚስት በኩል 2 በድምሩ 4 ምስክሮች በማቅረብ ጋብቻው አሁን በሚኖሩበት መደበኛ መኖሪያ ቦታ አቅራቢያ በሚገኝ ዝቅተኛው የአስተዳደር ጽህፈት ቤት ይመዘገባል፡፡
12. አንዲት ሴት በብቸኝነት ለመኖር በህግ የተወሰነው ጊዜ ሳያልፍ ከሌላ ወንድ ጋር ጋብቻ መፈፀም አትችልም፡፡
13. የሚፀና ጋብቻ ተፈፀመ የሚባለው ተጋቢዎቹ ለመጋባት ነፃና ሙሉ ፈቃዳቸውን ሲሰጡ ብቻ ነው፡፡
14. በሙሽራው በኩል 2 በሙሽሪት በኩል 2 በድምሩ 4 ምስክሮች መቅረብ አለባቸው፡፡

## 61. ደጋፊ ማስረጃዎች

1. ጋብቻው የሚፈፀመው በተጋቢ ወላጆች ወይም በቅርብ ዘመዶች መደበኛ መኖሪያ ቦታ ከሆነ የወላጆች ወይም የቅርብ ዘመዶች የነዋሪነት/ብሄራዊ መታወቂያ ወይም ከዝቅተኛው የአስተዳር ጽህፈት ቤት የተሰጠ የነዋሪነት ማስረጃ መቅረብ አለበት።
2. የተጋቢ ምስክሮች አገልግሎቱ ያላለፈበት የነዋሪነት/ብሄራዊ ወይም ፓስፖርት ወይም የመከላከያ ሰራዊት መታወቂያ ወይም ማንነታቸውን የሚገልጽ ማስረጃ መቅረብ አለበት፡፡
3. ሙሽራው/ዋ ከዚህ በፊት አግብቶ/ታ የፈታ/ች ከሆነ የፍቺ ምስክር ወረቀት ካለ መቅረብ አለበት፡፡
4. ሙሽራው/ዋ ከዚህ በፊት አግብቶ/ታ የሞተችበት/ባት ከሆነ የሞት ምስክር ወረቀት ካለ መቅረብ አለበት፡፡
5. ከ 6 ወር ወዲህ በተመሳሳይ ጊዜ የተነሱት ሁለት ሁለት 3 በ 4 ሳ.ሜ. የሆነ የተጋቢዎች ፎቶ-ግራፍ መቅረብ አለበት፡፡
6. በሃይማኖታዊ እና ባህላዊ ስርዓት የተፈፀመ ጋብቻ የተጋቢዎች ምስክሮች ወይም በጋብቻ ስርዓቱ ላይ የታደመ ሰው በክብር መዝገብ ሹሙ ፊት በአካል ቀርበው ፊርማቸውን ማኖር አለባቸው፡፡

7. የተጋቢዎች የልደት ምስክር ወረቀት ካለ መቅረብ አለበት፡፡

## 62. የክብር መዝገብ ሹም ፊት የሚፈጸም ጋብቻ አፈፃፀም ቅደም ተከተል

1. የክብር መዝገብ ሹሙ መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎችና ደጋፊ ማስረጃዎች መሟላታቸውን በመጠየቅ ያረጋግጣል፡፡
2. ጋብቻው ሁለቱ ተጋቢዎች እና ከእያንዳንዱ ተጋቢ በኩል ሁለት ሁለት ምስክሮች በተገኙበት በግልጽ ይፈፀማል፡፡
3. ተጋቢዎችና ምስክሮቹ የመሃላ ቃል ከመስጠታቸው በፊት የሚሰጡት ቃል ስለሚያስከትለው ሃላፊነት የክብር መዝገብ ሹሙ በግልጽ ማስረዳት አለበት፡፡
4. ተጋቢዎችና ምስክሮቹ ጋብቻ ለመፈጸም አስፈላጊ ሁኔታዎች አለመጣሳቸውን በጽሁፍ በሰፈረ ቃለ መሃላ ያረጋግጣሉ፡፡
5. ሁለቱም ተጋቢዎችና ምስክሮቻቸው በክብር መዝገብ ላይ መፈረም አለባቸው፡፡
6. የክብር መዝገብ ሹሙ ተጋቢዎቹ በህጋዊ ጋብቻ የተሳሰሩ መሆናቸውን አስታውቆ ለተጋቢዎቹ የጋብቻ ምስክር ወረቀት ይሰጣቸዋል፡፡

### ንዑስ ክፍል ሁለት

### መለያ ቁጥር

## 63. የጋብቻ ክብር መዝገብ ቅጽ ቁጥር

የጋብቻ የክብር መዝገብ ቅጽ ቁጥር በህትመት ወቅት ለቅጹ የተሰጠ ቁጥር ነው፡፡

## 64. የምዝገባ ጽ/ቤት መለያ ቁጥር

የፌደራል ኤጀንሲ ከክልሎች ጋር በመተባበር በሚያወጣው ዝርዝር ኮድ መሰረት ይመዘገባል፡፡

## 65. የጋብቻ ምዝገባ ልዩ መለያ ቁጥር፤

አንቀጽ 64 ስር የተመዘገበውን የምዝገባ ጽህፈት ቤት መለያ ቁጥር፣ የምዝገባው ዓመት ምህረት በአራት አህዝ ሆኖ በቁጥር እና የጋብቻውን መለያ ተራ ቁጥር በአራት አህዝ ሆኖ በቁጥር ቅደም ተከተል ይመዘገባል፡፡

## 66. የሙሽሮች የልደት ምዝገባ ልዩ መለያ ቁጥር

ልደቱ በአዋጅ ቁጥር 760/2004 መሠረት የተመዘገበ ከሆነ የሙሽሮችን የልደት ምዝገባ ልዩ መለያ ቁጥር ከልደት ምስክር ወረቀት ላይ በመውሰድ ይመዘገባል፡፡ ሆኖም በቀድሞው አሠራር የተሰጠ የልደት ምስክር ወረቀት መለያ ቁጥርን አይጨምርም፡፡

# ንዑስ ክፍል ሦስት

# ተጋቢዎችን በተመለከተ

## 67. ስም፣ የአባት ስም እና የአያት ስም

ስም፣ የአባት ስምና የአያት ስም በቅደም ተከተላቸው ከነዋሪነት/ብሔራዊ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ላይ በመውሰድ ይመዘገባል፡፡

# ንዑስ ክፍል አራት

# ጋብቻውን በተመለከተ

## 68. የተፈጸመበት ወር፣ ቀን እና ዓመተ ምህረት

ጋብቻው የተፈፀመበት ወር በፊደል፣ ቀን በሁለት አሀዝ ሆኖ በቁጥር እና ዓመተ ምህረት በአራት አሀዝ ሆኖ በቁጥር ይመዘግባል፡፡

## 69. የተፈጸመበት የጋብቻ ስርዓት

ተጋቢዎች በየትኛው የጋብቻ ስርዓት እንደተጋቡ የሚያቀርቡትን ማስረጃ በማየት የጋብቻ ስርዓቱን የሲቪል ወይም ሃይማኖታዊ ወይም ባህላዊ ጋብቻ ተብሎ ይመዘገባል፡፡

# ንዑስ ክፍል አምስት

# የሙሽሮች ምስክሮችን በተመለከተ

## 70. ስም፣ የአባት ስም እና የአያት ስም

ስም፣ የአባት ስም እና የአያት ስም ከነዋሪነት/ብሄራዊ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ላይ በማየት ይመዘገባል፡፡

## ክፍል ሰባት

## የፍቺ ምዝገባ

## ንዑስ ክፍል አንድ

## በፍቺ ምዝገባ ወቅት ማሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎችና ደጋፊ ማስረጃዎች

### 71. ቅድመ ሁኔታዎች

1. የተፋቺዎች መረጃ ከፍርድ ቤት ውሳኔ ግልባጭ ላይ ተወስዶ ይመዘገባል፤ ሆኖም ያልተሟላ መረጃ ሲኖር አስመዝጋቢዎች በተለያየ ጊዜ ቢመጡም ተጠይቆ ይሞላል፡፡

### 72. ደጋፊ ማስረጃዎች

1. ፍቺው ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት የተከናወነ መሆኑን የሚገልፅ የፍርድ ቤት ውሳኔ ግልባጭ መቅረብ አለበት፡፡
2. ፍቺው የሚመዘገበው በወኪል ከሆነ የፍቺ ልዩ ውክልና ማስረጃ መቅረብ አለበት፡፡
3. ቀደም ሲል የጋብቻ ምስክር ወረቀት የተሰጠ ከሆነ የተሰጠው የጋብቻ ምስክር ወረቀት መመለስ አለበት፤

## የፍቺ ክብር መዝገብ ቅጽ ዝርዝር መረጃ አመዘጋገብ

## ንዑስ ክፍል ሁለት

## መለያ ቁጥር

### 73. የፍቺ ክብር መዝገብ ቅጽ ቁጥር

የፍቺ ክብር መዝገብ ቅጽ ቁጥር በህትመት ወቅት ለቅጹ የተሰጠ ቁጥር ነው፡፡

### 74. የምዝገባ ጽ/ቤት መለያ ቁጥር

የፌደራል ኤጀንሲ ከክልሎች ጋር በመተባበር በሚያወጣው ዝርዝር ኮድ መሰረት ይመዘገባል፡፡

### 75. የፍቺ ምዝገባ ልዩ መለያ ቁጥር

በአንቀጽ 74 የተመዘገበውን የምዝገባ ጽህፈት ቤት መለያ ቁጥር፣ የምዝገባው ዓመተ ምህረት በአራት አሀዝ ሆኖ በቁጥር እና የፍቺውን መለያ ተራ ቁጥር በአራት አሀዝ ሆኖ በቁጥር በቅደም ተከተል ይመዘገባል፡፡

## 76. የተፋቺዎች የልደት ምዝገባ ልዩ መለያ ቁጥር

ልደቱ በአዋጅ ቁጥር 760/2004 መሰረት የተመዘገበ ከሆነ የተፋቺዎች የልደት ምዝገባ ልዩ መለያ ቁጥር ከልደት ምስክር ወረቀት ላይ በመወሰድ ይመዘገባል፡፡

## ንዑስ ክፍል ሦስት

## ተፋቺዎችን በተመለከተ

## 77. ስም፣ የአባት ስም እና የአያት ስም

ስም፣ የአባት ስም እና የአያት ስም በቅደም ተከተላቸው ከነዋሪነት/ብሔራዊ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ላይ በማየት ይመዘገባል፡፡

## ንዑስ ክፍል አራት

## ፍቺውን በተመለከተ

## 78. የፈረሰው ጋብቻ የተፈጸመበት ወር፣ ቀን እና ዓመተ ምህረት

የፈረሰው ጋብቻ የተፈጸመበት ወር ስም በፊደል፣ ቀን በሁለት አሀዝ ሆኖ በቁጥር እና ዓመተ ምህረት በአራት አሀዝ ሆኖ በቁጥር ከጋብቻ ምስክር ወረቀት ላይ በማየት ይመዘገባል፡፡ የጋብቻ ምስክር ወረቀት ካልተገኘ አስመዝጋቢውን በመጠየቅ ይመዘገባል፡፡

## 79. የፈረሰው ጋብቻ የተፈጸመበት ቦታ

የፈረሰው ጋብቻ የተፈጸመበት ቦታ ክልል/ከተማ አስተዳደር፣ ዞን/ከተማ አስተዳደር፣ ከተማ፣ ክፍለ ከተማ፣ ወረዳ/ልዩ ወረዳ እና ቀበሌ ስም/ቁጥር ከጋብቻ ምስክር ወረቀት ላይ በማየት ይመዘገባል፡፡ የጋብቻ ምስክር ወረቀት ካልተገኘ አስመዝጋቢ በመጠየቅ ይመዘገባል፡፡

## 80. የፍቺው ምክንያት

የፍቺው ምክንያት ከፍርድ ቤት የፍቺ ውሳኔ ብቻ ተወስዶ የሚመዘገብ ይሆናል፡፡

## 81. ፍቺው የተፈጸመበት ወር፣ ቀን እና ዓመተ ምህረት

ፍቺው የተፈጸመበት ወር ስም በፊደል፣ ቀን በሁለት አሀዝ ሆኖ በቁጥር እና ዓመተ ምህረት በአራት አሀዝ ሆኖ በቁጥር ከፍርድ ቤት በቀረበ የፍቺ ውሳኔ ግልባጭ ማስረጃ ላይ በማየት ይመዘገባል፡፡

### 82. ፍቺውን የወሰነው ፍርድ ቤት ስም እና የፍርድ ቤት መዝገብ ቁጥር

ፍቺውን የወሰነው ፍርድ ቤት ስምና የፍርድ ቤት መዝገብ ቁጥር ከቀረበው የፍርድ ቤት የፍቺ ውሳኔ ግልባጭ ማስረጃ በማየት ይመዘገባል፡፡

### 83. በፈረሰው ጋብቻ ውስጥ ይተዳደሩ የነበሩ ህፃናት ብዛት

ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ በህይወት ያሉ በተፋቺዎች ሥር ይተዳደሩ የነበሩ ህፃናት ብዛት ፍቺውን ከሚያስመዘግበው ተጠይቆ በፊደል ይመዘገባል፡፡

## ክፍል ስምንት

## የሞት ምዝገባ

## ንዑስ ክፍል አንድ

## ለሞት ምዝገባ የሚያስፈልጉ ደጋፊ ማስረጃዎች

### 84. ደጋፊ ማስረጃዎች

1. የሟች የነዋሪነት ወይም ብሄራዊ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ወይም ስደተኛነቱን የሚገልጽ ማስረጃ ወይም የመኖሪያ ፍቃድ ካለ መቅረብ አለበት፡፡
2. አስመዝጋቢው ጊዜው ያላለፈበት ማንነቱን የሚገልጽ መታወቂያ ማቅረብ አለበት።
3. ሞቱን የሚያስመዘግበው ፖሊስ ማንነቱን የሚገልጽ መታወቂያ/ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡
4. ሞቱ የሚመዘገበው በግለሰቡ መጥፋት ውሳኔ ምክንያት ከሆነ የፍርድ ቤት ውሳኔ ትክክለኛ ቅጂ መቅረብ አለበት፡፡
5. የጊዜ ገደቡ ላለፈ የሞት ምዝገባ ስለሞቱ መከሰት የሚገልፅ የፅሑፍ ማስረጃ መቅረብ አለበት፡፡
6. ሞቱ የተከሰተው በውጭ አገር ዜጋ ላይ ከሆነ ከጤና ተቋም የተሰጠ የሞት ማሳወቂያ ወረቀት ወይም ማስረጃ መቅረብ አለበት፡፡

## ንዑስ ክፍል ሁለት

## የሞት ክብር መዝገብ ቅጽ ዝርዝር መረጃ አመዘጋገብ

## መለያ ቁጥር

### 85. የሞት ክብር መዝገብ ቅጽ ቁጥር

የሞት ክብር መዝገብ ቅጽ ቁጥር በህትመት ወቅት ለቅጹ የተሰጠ ቁጥር ነው፡፡

## 86. የምዝገባ ጽህፈት ቤት መለያ ቁጥር

ኤጀንሲው አግባብ ካለው የክልል አካል ጋር በመተባበር በሚያወጣው ዝርዝር ኮድ መሰረት ይመዘገባል፡፡

## 87. የሞት ምዝገባ ልዩ መለያ ቁጥር

ከላይ በአንቀጽ 86 ላይ የተመዘገበውን የምዝገባ ጽህፈት ቤት መለያ ቁጥር፣ የምዝገባው ዓመተ ምህረት በአራት አህዝ ሆኖ በቁጥር እና የሞቱን መለያ ተራ ቁጥር በአራት አህዝ ሆኖ በቁጥር በቅደም ተከተል ይመዘገባል፡፡

## 88. የልደት ምዝገባ ልዩ መለያ ቁጥር

ልደቱ በአዋጅ ቁጥር 760/2004 መሠረት የተመዘገበ ከሆነ የሟችን የልደት ምዝገባ ልዩ መለያ ቁጥር ከልደት ምስክር ወረቀት ላይ በመውሰድ ይመዘገባል፡፡ ሆኖም በቀድሞው አሠራር የተሰጠ የልደት ምስክር ወረቀት መለያ ቁጥርን አይጨምርም፡፡

### ንዑስ ክፍል ሶስት

### ሟችን በተመለከተ

## 89. ስም፣ የአባት ስም እና የአያት ስም

ስም፣ የአባት ስም እና የአያት ስም በቅደም ተከተላቸው ከነዋሪነት /ብሔራዊ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ላይ በማየት ወይም አስመዝጋቢውን በመጠየቅ ይመዘገባል፡፡

## 90. የነዋሪነት/ብሄራዊ መታወቂያ ቁጥር

የሟች ማንነቱን የሚገልጽ  መታወቂያ ካለ ቁጥሩ ተወስዶ ይመዘገባል።

## 91 ማዕረግ

ሟች ከመሞቱ በፊት የነበረውን ማዕረግ ከመታወቂያው ወይም አስመዝጋቢውን በመጠየቅ ይመዘገባል፡፡ ሆኖም ግን ሟች ሲሞት ማዕረግ የሌለው ከሆነ በሰረዝ ምልክት (-) ይታለፋል፡፡

## 92. ፆታ

የሟች ፆታ ከመታወቂያው ወይም ከአስመዝጋቢው ተጠይቆ ወንድ ከሆነ “ወንድ”፣ ሴት ከሆነች “ሴት” በማለት ይመዘገባል፡፡

## 93. ዕድሜ

የሟች ዕድሜ ከሟች የልደት ምስክር ወረቀት ወይም ከነዋሪነት/ብሄራዊ መታወቂያ ወይም ከፓስፖርት ላይ በማየት ወይም ከአስመዝጋቢ ተጠይቆ ባጠናቀቀው ዓመት የሚመዘገብ ይሆናል፡፡ ሆኖም ግን የሟች ዕድሜ፡-

1. ከ1 ዓመት በታች ከሆነ ባጠናቀቀው ሙሉ ወራት ይመዘገባል፣
2. ከ1 ወር በታች ከሆነ በቀናት ይመዘገባል፣
3. ከ1 ቀን በታች ከሆነ በሰዓታት ይመዘገባል፡፡

### ንዑስ ክፍል አራት

### ሞቱን በተመለከተ

## 94. የተከሰተበት ወር፣ ቀን እና ዓመተ ምህረት

ሞቱ የተከሰተበትን ወር ስም በፊደል፣ ቀን በሁለት አሀዝ ሆኖ በቁጥር እና ዓመተ ምህረት በአራት አሀዝ ሆኖ በቁጥር ይመዘገባል፡፡

## 95. የተከሰተበት ስፍራ/ተቋም/ ዓይነት

1. ሟች የሞተው በጤና ተቋም ከሆነ የተቋሙ ስም፣ ዓይነት (ሆስፒታል /ጤና ጣቢያ/ ክሊኒክ/ጤና ኬላ) እና ባለቤትነት (የመንግስት/መንግስታዊ ያልሆነ እና የግል) ለአስመዝጋቢው ከተሰጠው ማሳወቂያ ቅጽ ላይ ተወስዶ ይመዘገባል፡፡
2. ሟች ህይወቱ ያለፈው ከጤና ተቋም ውጪ ከሆነ ከአስመዝጋቢው ተጠይቆ በመኖሪያ ቤት ወይም በጋራ መኖሪያ ቤት ወይም በጎዳና ላይ ተብሎ ይመዘገባል፤ ከነዚህ ቦታዎች ውጪ ከሆነም ቦታው ተጠቅሶ ይመዘገባል፡፡

## 96. የተከሰተበት ቦታ/ሀገር

ሞቱ የተከሰተበትን ልዩ ስምና ቦታው የሚገኝበትን ክልል፣ ዞን/ከተማ አስተዳደር፣ ከተማ፣ ክፍለ ከተማ፣ ወረዳ/ልዩ ወረዳ እና አስተዳደር ጽህፈት ቤት ስም/ቁጥር ይመዘገባል፡፡ ሞቱ የተከሰተው በውጭ ሀገር ከሆነ የሀገሩ ስም ይመዘገባል፡፡

## 97. የሞት ምክንያት

የሞት ምክንያት ከጤና ተቋም ከሚመጣ የሞት ምክንያት ምዝገባ ማስረጃ ብቻ ተወስዶ የሚመዘገብ ሆኖ፡-

1. በክብር መዝገቡ ተራ ቁጥር 18 (1) ላይ ባለው ክፍት ቦታ ላይ የሚሞላው የሞት ምክንያት መረጃ ከጤና ተቋም ከመጣው የሞት ምክንያት ማስረጃ ተራ ቁጥር 1 ላይ ከተሞላው በመውሰድ በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባል፡፡

2. በክብር መዝገቡ ተራ ቁጥር 18 (2) ላይ ባለው ክፍት ቦታ ላይ የሚሞላው የሞት ምክንያት መረጃ ከጤና ተቋም ከመጣው የሞት ምክንያት ማስረጃ ተራ ቁጥር 2 ላይ ከተሞላው በመውሰድ በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባል፡፡
3. በክብር መዝገቡ ተራ ቁጥር 18 (3) ላይ ባለው ክፍት ቦታ ላይ የሚሞላው የሞት ምክንያት መረጃ ከጤና ተቋም ከመጣው የሞት ምክንያት ማስረጃ ተራ ቁጥር 3 ላይ ከተሞላው በመውሰድ በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባል፡፡
4. ከላይ ከተዘረዘሩት ከሦስቱ አንዱ ያልተሞላ የሞት ምክንያት ሲያጋጥም በሰረዝ ምልክት (-) ይታለፋል፡፡

## 98. ለሞት ምክንያት የተሰጠ ማስረጃ አይነት

ለሞት ምክንያት የተሰጠው የማስረጃ ዓይነት ከጤና ተቋም ከተሰጠው ማስረጃ ላይ በመውሰድ ይመዘገባል፡፡ የማስረጃው አይነት ሲባል በቃል መጠይቅ (ቨርባል አውቶፕሲ) እና በህክምና ምርመራ የተገኘ ማስረጃ ማለት ነው፡፡

## 99. ለሞት ምክንያት የተሰጠ ማስረጃ ቁጥር

የሞት ምክንያት ማስረጃ ቁጥር ከጤና ተቋም ከተሰጠው ማስረጃ ላይ በመውሰድ ይመዘገባል፡፡

## 100. ሟች የሞተችው በእርግዝና ወቅት /በወሊድ ወቅት/ ከወሊድ በኋላ ባሉት 42 ቀናት ውስጥ ነው? ___________________

1. ሟች የሞተችው በእርግዝና ወቅት ከሆነ "**በእርግዝና ወቅት**" ወይም በወሊድ ወቅት ከሆነ "**በወሊድ ወቅት**" ወይም ከወሊድ በኂላ ባሉት 42 ቀናት ውስጥ ከሆነ "**ከወሊድ በኂላ ባሉት 42 ቀናት ውስጥ**" ከሚሉት አማራጮች ስር ትክክለኛውን አማራጭ አስመዝጋቢውን በመጠየቅ በተሰጠው መልስ ስር በማስመር በክፍት ቦታ ላይ " **አዎ** " ተብሎ ይመዘገባል፡፡
2. ሟች የሞተችው በንዑስ ቁጥር አንድ ከተጠቀሱት ምክንያቶች ውጭ ከሆነ ግን ምንም ሳይሰመር በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ "**አይደለም**" ተብሎ ይመዘገባል፡፡

## 101. ቀብሩ የተፈፀመበት ስፍራ

የሟች ቀብር የተፈፀመበትን ልዩ ስፍራ ከአስመዝጋቢው በመጠየቅ ይመዘገባል፡፡

## ንዑስ ክፍል አምስት

## አስመዝጋቢን በተመለከተ

### 102. የአስመዝጋቢው ሙሉ ስም

ስም፣ የአባት ስምና የአያት ስም ከአስመዝጋቢው የነዋሪነት ወይም ብሄራዊ መታወቂያ ወይም ፓስፓርት ላይ በመውሰድ ይመዘግባል፡፡

### 103. ከሟች ጋር ያለ ዝምድና

አስመዝጋቢው ከሟች ጋር ያለውን ዝምድና ተጠይቆ ይመዘገባል፡፡

## ክፍል ዘጠኝ

## የምስክር ወረቀት አዘገጃጀትና አሰጣጥ

### 104. የምስክር ወረቀት አዘገጃጀት

የጋብቻ ምዝገባ ምስክር ወረቀት ለማዘጋጀት ከእያንዳንዳቸው ተጋቢዎች 3በ4 የሆነ

በተመሳሳይ ወቅት የተነሱት ሁለት ሁለት ፎቶ ግራፍ መቅረብ አለበት፡፡

### 105. የምስክር ወረቀት አሰጣጥ

ተመዝጋቢው/አስመዝጋቢው ወይም ህጋዊ ውክልና የተሰጠው አካል ማንነቱን የሚገልፅ የነዋሪነት/ ብሄራዊ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ይዞ ሲቀርብ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

### 106. በቀድሞ ህጎች የተሰጡ የወሳኝ ኩነት ማስረጃዎችን በተመለከተ

በቀድሞ ህግ ወይም ልማዳዊ አሰራሮች  በተካሄዱ ምዝገባዎች የተገኘ የምስክር ወረቀት በመጥፋቱ ወይም በመበላሸቱ ወይም ከአገልግሎት ውጪ በመሆኑ ምክንያት የምትክ ወይም የይመሳከርልኝ ጥያቄ ሲቀርብ  የቀድሞ የክብር መዝገብ የሌለ እንደሆነ አዲስ ምዝገባ ተከናውኖ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

## ክፍል አስር

## የመረጃ አደረጃጀት፣ቅብብሎሽ፣ አያያዝና አቅርቦት

## ንዑስ ክፍል አንድ

## የምዝገባ መረጃ

### 107. መረጃ ስለማጠናቀር፣ ስለማስተላለፍና አጣርቶ ስለመቀበል

1. የተመዘገቡ መረጃዎችን በየወሩ በኩነቱ ዓይነት  በሁለት ኮፒ በማጠናቀር የምዝገባ ቅጂዎች ለሚቀጥለው የወሳኝ ኩነት ምዝገባ መዋቅር መላክ አለበት፡፡
2. አንዱን የጥንቅር መረጃ  ከቅጂዎች ጋር ቀጥሎ ላለው የወሳኝ ኩነት መዋቅር መላክ አለበት፡፡ ሁለተኛውን ኮፒ በአግባቡ አደራጅቶ ይይዛል፡፡

3. ተረካቢ መዋቅሮች በተዘጋጀው የመረካከቢያ ፎርም መሰረት ከታችኛው የምዝገባ መዋቅር የተላኩ መረጃዎችን ወይም ቅጂዎችን በኩነት ዓይነት ቆጥሮ መረከብ አለባቸው፡፡
4. በቅጂዎች የተመዘገቡ መረጃዎች የተሟሉና ትክክለኛ መሆናቸው በየደረጀው ባለ መዋቅር መጣራት አለበት፡፡
5. በተለያዩ ግድፈቶች ምክንያት ተሟልተውና ተስተካክለው እንዲመጡ ወደየመዋቅሩ ተመላሽ የተደረጉ ቅጂዎች በተላከው ፎርማትና በተቀመጠው የጊዜ ገደብ የማይመለሱ ከሆነ በቅጂዎች ያለመመለስ ምክንያት ለሚፈጠሩ ችግሮች ሃላፊነት ይወስዳል፡፡

## 108. የክብር መዝገብ /ቅጂዎች/ ስለማደራጀት

1. እያንዳንዱ የክብር መዝገብ በኩነት ዓይነትና በዓመተ ምህረት በተዘጋጀው ሼልፍ ላይ በጥንቃቄ ያስቀምጣል፡፡ የክብር መዝገብ መለያ ቁጥሩን በሼልፉ ላይ ይፅፋል፡፡ በቴክኖሎጂ ተደራጅቶ መያዝ አለበት፡፡
2. ከክብር መዝገብ ተለይተው ወደ ክልል መዝጋቢ አካላትና በፌዴራሉ ኤጀንሲ የሚመጡ ቅጂዎች በዓመተ ምህረት፣ በኩነት ዓይነት፣ በክልል፣ በዞን /በክፍለ ከተማ/፣ በወረዳ በመለየት መደራጀት አለበት፡፡
3. የተደራጀውን መረጃ ለመፈለግ ያመች ዘንድ በፌዴራሉ ኤጀንሲና በክልል መዝጋቢ አካላት የማውጫ መዝገብ መዘጋጀት አለበት፡፡ በማውጫው መዝገብ ላይ የክብር መዝገቡ በዓመተ ምህረት፣ በኩነት ዓይነት፣ በምዝገባ ቦታ እና በሼልፍ ቁጥር ይሰፍራል፡፡

## 109. መረጃ ለመውሰድ ሊሟሉ የሚገቡ ቅድመ ሁኔታዎች

1. መረጃውን እንዲጠቀም በህግ የተፈቀደለት አካል ስለመሆኑ በሚያቀርበው ደብዳቤ መረጋገጥ አለበት፡፡
2. መረጃው ለጥናትና ምርምር ዓላማ የሚፈለግ ከሆነ ይህንን የሚገልጽ ጥያቄ ቀርቦ በሚመለከተው ኃላፊ ሲፈቀድ ተገልጋዩ ፎርም መሞላቱን የክብር መዝገብ ሹሙ ማረጋገጥ አለበት፡፡
3. መረጃ ጠያቂው ተቋም ከሆነ የተወካዩ የታደሰ መታወቂያና ደብዳቤ፣ ግለሰብ ከሆነ የግለሰቡ የታደሰ መታወቂያ መቅረብ አለበት፡፡

## 110. የመረጃዎችን እንቅስቃሴ አስመልክቶ ሊወሰድ ስለሚገባው ጥንቃቄ

መረጃዎች በስራ ምክንያት በየደረጃው ባሉት የወሳኝ ኩነቶች መዝጋቢ አካላት መካከል ወይም በአንድ መዝጋቢ አካል ውስጥ በሚገኙ የስራ ክፍሎች በሚንቀሳቀሱበት ጊዜ ጥንቃቄ ሊወሰድ የሚገባ ሲሆን፡-

1. አስረካቢና ተረካቢ መተማመኛ መፈራረም አለባቸው፡፡
2. መረጃው የጠፋ ወይም ከሌሎች መረጃዎች መካከል ተፈልጎ ያልተገኘ እንደሆነ የሚመለከተው ወይም ኃላፊነት የተሰጠው ባለሙያ ሃላፊነት ይወስዳል፡፡

## 111. የክብር መዝገቦችን/መረጃዎችን ደህንነታቸውን ስለመጠበቅ፣

1. የመረጃ ማስቀመጫ ሼልፍ ደረጃውን ከጠበቀ ቁሳቁስ መዘጋጀት አለበት፡፡
2. ሼልፉ በቁልፍ የሚቆለፍና ቁልፍንም በሃላፊነት ከሚመለከተው ባለሙያ ውጪ መያዝ የለበትም፡፡
3. የተጐዱና የተጐሳቆሉ የክብር መዝገቦችና ቅጂዎች ሲያጋጥሙ መታደስና መጠገን አለባቸው፡፡
4. የወሳኝ ኩነት ምዝገባ መረጃዎች በተተኪ አኑር /ባክ አፕ/ ደህንነታቸው ተጠብቆ መያዝ አለበት፡

## 112. የማመሳከር አገልግሎት ለመስጠት መሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች፣

1. ተገልጋዩ ከዚህ በፊት የወሰደውን ዋናውን ማስረጃ እና ማንነቱን የሚገልጽ ጊዜው ያላለፈበት ማስረጃ ዋናውንና ኮፒ ወይም ተገልጋዩ የውጪ ዜጋ ከሆነ ፓስፖርትና ቪዛ ይዞ  መቅረብ አለበት፡፡
2. በውክልና ከሆነ በንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰው እና ህጋዊ የውክልና ማስረጃ መቅረብ አለበት፡፡
3. ቅድመ ሁኔታ ማሟላቱን በማረጋገጥ በሠርቲፊኬቱ ጀርባ ላይ ትክክለኛ ስለመሆኑ በማህተም እና ፊርማ እንዲሁም ያመሳካሪው ስም እና ቲተር መደረግ አለበት፡፡

## ክፍል አስራ አንድ

## ልዩ ልዩ ድንጋጌ

## 113. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሌሎች ህጐች

1. የወሳኝ ኩነት ምዝገባ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 2/2008፣ 4/2009፣ 5/2009 እና የወሳኝ ኩነት ምዝገባ መረጃ አደረጃጀት፣ ቅብብሎሽ፣ አያያዝ እና አቅርቦት አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 3/2008 ተሽረው በዚህ መመሪያ ተተክተዋል።
2. የህን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም አሰራር ወይም ሰርኩላር ደብዳቤ በዚህ መመሪያ ውስጥ የተመለከተ ጉዳዮችን በሚመለከት ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

## 114. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከ15/5/2010 ዓ.ም ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ15/5/ 2010 ዓ.ም**

**ኤልሳ ተስፋይ**

**የፌደራል ወሳኝ ኩነት ምዝገባ ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር**